በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# የእምነት ሕይወት - የመጨረሻ ክፍል ፮

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf : www.zeorthodox.org

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ሚያዝያ ፳፫ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.**

# <u>የእምነት ሕይወት - የመጨረሻ ክፍል ፲</u>

## <u>*የእምነታችን መፈተን*</u>

## በሃይማኖት እየኖርን ነው?

- በሃይማኖት የምንኖር ከሆንን እምነታችን በብዙ መንገዶች ይፈተናል፡፡
- ሐዋርያት ስለ ሃይማኖት ከመጻፍና ከማስተማር በተጨማሪ እንዲህ ብለውናል፡፡

1. **እምነት በፍቅር ራሱን እንደሚገልጥም ጽፈውልናል፡፡ *<u>ገላ 5:6፡፡</u>***

- **ሐዋርያው *<u>በቀዳ ቆሮ 13</u>*** ‹‹ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፥ አይታበይም፤ የማይገባውን አያደርግም፥ የራሱንም አይፈልግም፥ አይበሳጭም፥ በደልን አይቆጥርም፤ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤ ሁሉን ይታገሣል፥ ሁሉን ያምናል፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይጸናል። ›› **በማለት እንደጻፈልን በፍቅር የሚሠራ እምነት አለን?**
- **ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ** ‹‹ትንቢትም ቢኖረኝ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ፥ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ።›› ***<u>ቀዳ ቆሮ 13:2፡፡</u>*** **እንዳለን እምነት የሚፈተንበት አንዱ መንገድ ፍቅር ነው፡፡**

2. **እምነት በሥራ ይፈተናል**

- **ሐዋርያው** ‹‹አንተ እምነት አለህ እኔም ሥራ አለኝ፤ እምነትህን ከሥራህ ለይተህ አሳየኝ፥ እኔም እምነቴን በሥራዬ አሳይሃለሁ ይላል።›› ***<u>ያዕ 2:18፡፡</u>*** **እንዳለው እምነት ሙት ወይም ሕያው መሆኑ የሚመዘነው በሥራ ነው፡፡ *<u>ያዕ 2:20፡፡</u>* ከሥራ የተለየም እምነት የሞተ ማዳንም የማይችል እምነት ነው፡፡**

# የእምነት ሕይወት - የመጨረሻ ክፍል ፯

2. **እምነት በሥራ ይፈተናል**

- **ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ስለ ሥራና እምነት አስፈላጊነት**‹‹እግዚአብሔርን እንዲያውቁ በግልጥ ይናገራሉ፥ ዳሩ ግን የሚያስጸይፉና የማይታዘዙ ለበጎ ሥራም ሁሉ የማይበቁ ስለ ሆኑ፥ በሥራቸው ይክዱታል።›› ***ቲቶ 1:16*****፣ ለጢሞቴዎስም** ‹‹ነገር ግን ለእርሱ ስለ ሆኑት ይልቁንም ስለ ቤተ ሰዎቹ የማያስብ ማንም ቢሆን፥ ሃይማኖትን የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው።›› ***ቀዳ ጢሞ 5:8*****፣ ባልቴቲቱም በክርስቶስ ያላትን እምነት ማጉደልዋን አስመልክቶ** ‹‹የፊተኛውንም እምነታቸውን ስለ ናቁ ይፈረድባቸዋል፡፡›› ***ቀዳ ጢሞ 5:12*****፣ ንጽሕና በጎደለውና ሐሰት በነገሠበት ሁኔታ ለመኖር የሚወዱትንም አስመልክቶ** ‹‹ይህ እውቀት አለን ብለው፥ አንዳንዶች ስለ እምነት ስተዋልና። ጸጋ ከአንተ ጋር ይሁን።›› ***ቀዳ ጢሞ 6:21*** **በማለት ስለ እምነታችን በሥራ መፈተን እንዳለ ጽፎልናል፡፡**
- **ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም** ‹‹አውቄዋለሁ የሚል ትእዛዛቱንም የማይጠብቅ ውሸተኛ ነው እውነትም በእርሱ ውስጥ የለም። ቃሉን ግን የሚጠብቅ ሁሉ በእርሱ የእግዚአብሔር ፍቅር በእውነት ተፈጽሞአል። በእርሱ እንዳለን በዚህ እናውቃለን፤ በእርሱ እኖራለሁ የሚል እርሱ እንደ ተመላለሰ ራሱ ደግሞ ሊመላለስ ይገባዋል።›› ***ቀዳ ዮሐ 2:4-6፡፡*** **በማለት ጽፎልናል፡፡**

3. **እምነት በልብ ንጽሕናም ይፈተናል**

- **እግዚአብሔር በፊቱ እንደሆነ፣ ኃጢአትን እንደሚጠላ ቅዱስ፣ ለሁሉም እንደሥራው የሚከፍለው የፍትሕ አምላክ መሆኑን የማያምን ሰው** ‹‹በእርሱ የሚኖር ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም፤ ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ አላየውም አላወቀውምም።›› ***ቀዳ ዮሐ 3:6*** **እንደተጻፈው በሚወደው በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአትን ከመሥራት አይቆጠብም፡፡**
- **የሚበድል ሰው እግዚአብሔር እንደሚያየው፣ እንደሚሰማው እንደላመነው እንደ ሄሮድስ ነው፤ የሰዎችን ማባበል ተቀብሎ ተደስቶአልና፡፡** ***የሐዋ 12:21-23፡፡*** **የሚያምን ሰው ግን በሁሉ ይጻናል፡፡** ***ፊል 4:11፡፡***

# የእምነት ሕይወት - የመጨረሻ ክፍል ፲

4. **እምነት እግዚአብሔር የሚሳነው የለም ለማለት በሚያስችለው ኃይል ይፈተናል**

- ለእግዚአብሔር የሚሳነው የለም ብለን የምናምንበት ኃይል አለን? ‹‹ለሚያምን ሁሉ ይቻላል፡፡›› ***ማር 9፡23*** ተብለናልና፡፡
- የማይቻል ከባድ ነገር እንዳለ ይሰማን ይሆን? ‹‹ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ፡፡›› ***ፊል 4፡13*** እንበል፡፡ ተስፋ መቁረጥ የእምነትም ሆነ የተስፋ ተቃራኒ ነውና፡፡
- ራሳቸውን ያጠፉ ሰዎች መፍትሔ አናገኝም፣ ከሞት በኋላም ሕይወት የለም በማለት እምነታቸውንና ተስፋቸውን አጥተውታል፡፡
- ዛሬም በዙሪያቸው ለሚገጥሟቸው አንዳንድ ችግሮች እጃቸውን የሰጡ ሰዎችም የሚረዳቸው ኃይል እንዳለ የሚያምኑበትን ኃይል አጥተውታል፡፡
- እምነት ባለመጠራጠር ለሚይዙትና ለሚኖሩበት ሰዎች ኃይል ነው፡፡
- እምነት በአንዳንዶች ዘንድ በግያዝ እጅ የተያዘ ሀብት ነው፡፡ ሳያምኑበት መስቀሉን ብቻ እጃቸው በመያዝ ምልክት ሲያደርጉ ሲያማትቡ ለምናገኛቸው ለአንዳንዶችም እምነት በሰነፎች እጅ እንደወደቀ ገንዘብ ነው፡፡ *ካል ነገ 4፡31፡፡*
- ባሕረ ኤርትራ የተከፈለው የሙሴ በትር ብቻ ነው ወይስ በእግዚአብሔር ኃይል ታምኖ በትሩን ተሸክሞ የተራመደ ሙሴ በእግዚአብሔር ስም በሠራው ተአምራት?
- አንዳንዴ እንጸልያለን ነገር ግን ጸሎታችን እንደ ኤልያስ ተአምራትን ማድረግ የሚያስችለን ነው? በጸሎቱ ሰማይን ለጉሞአልና፡፡ እምነታችንን ባለን ጥንካሬና ኃይል እንፈትነው፡፡

# የእምነት ሕይወት - የመጨረሻ ክፍል ፲

5. **እምነት በጭንቀታችን ጊዜ በሚገጥሙን ነገሮች ይፈተናል**

- ሁሉም ሰው ይፈተናል፡፡ መፈተናችን ሰላማችንን የሚያሳጣን ከሆነ እምነታችን ደካማ ነው ማለት ነው፡፡ የሚያምን ሰው ፈተና ለእኛ መልካም እንዲሆንልን የተከሰተና እግዚአብሔርም መፍትሔ የሚሰጥበት እንደሆነ ያምናል፡፡
- ‹‹እግዚአብሔርን ለሚያምኑ እንደ አሳቡም ለተጠሩ ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን፡፡›› ሮሜ 8፡28፣ ‹‹ወንድሞቼ ሆይ፥ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ፥ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት›› ***ያዕ 1፡2-3፡፡*** እንደተባለ በፈተና ደስ ይበለን፡፡
- የሚያምን ሰው በፈተናውና በራሱ መከከል እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋል፡፡ ‹‹በጭንቃቸው ሁሉ እርሱ ተጨነቀ፥ የፊቱም መልአክ አዳናቸው በፍቅሩና በርኅራኄውም ተቤዣቸው፥ በቀደመውም ዘመን ሁሉ አንሥቶ ተሸከማቸው።›› ***ኢሳ 63፡9 ፡፡*** እንደተባለ ፈተናው ተኖ ሲጠፋ እግዚአብሔር ግን በፊታችን ሆኖ ይታየናል፡፡
- የሚያምን ሰው በሙሴ፣ በዮሴፍ፣ በዳዊት፣ በኢዮብ፣ በዳንኤል፣ በሦስቱ ሕጻናት የተደረገባቸውን እያሰበ ‹‹ነፍሳችን እንደ ወፍ ከአዳኞች ወጥመድ አመለጠች። ወጥመድ ተሰበረ እኛም አመለጥን። ረድኤታችን ሰማይንና ምድርን በሠራ በእግዚአብሔር ስም ነው።›› ***መዝ 123(124)*** እያለ በእግዚአብሔር ያለ እምነቱ ይጨምራል፡፡
- እግዚአብሔርም ፈተናውን በደስታ ስንቀበለው እኔም ደስ ይለኛል ይለናል፡፡ ሐዋርያት ‹‹እነርሱም ስለ ስሙ ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለ ተቈጠሩ ከሸንጎው ፊት ደስ እያላቸው ወጡ›› ***የሐዋ 5፡41፡፡*** እንዳሉ፡፡
- የሚያምን ኦርቶዶክሳዊ ሰው የተዘጉ ብዙ በሮችን ሳይሆን በእግዚአብሔር የተከፈቱ በሮችን ይመለከታል፡፡ የሰማይና የምድር ቁልፎች ባሉት ይታመናል፡፡ ***ራእ 3፡7፡፡*** ‹‹በሰማይ የተከፈተ ደጅም አየሁ፡፡›› ***ራእ 4፡1፡፡*** ይላል፡፡ አሁን የተዘጋ በር አለ እግዚአብሔር ግን ካመንን ስለእምነታችን ሲከፍተውም እናርፋለን፡፡

# <u>የእምነት ሕይወት - የመጨረሻ ክፍል ፮</u>

6. እምነት በትእዛቱም ይፈተናል

1. ሰው በእምነቱ ከሚፈተንባቸው ትእዛዛት አንዱ አሥራትን መክፈል ነው፡፡ ይልቁኑ አማንያን ገንዘብ የሚያስፈልገን ሆነን ያላችሁን ሽጣችሁ ተከተሉኝ ተብለን እንፈተናለን፡፡ የማያምን ሰው ሙሉ ደመወዙ ያልበቃኝ አሥራት ተቀንሶ እንዴት ይበቃኛል? ብሎ ሲጠራጠር የሚያምን ግን አሥራቱን ስሰጥ የተቀረው ገንዘብ ይባረክልኛል ብሎ ያምናል፡፡ <u>***ሚል 3፡10፡፡***</u>

- ለሚለምንህ ስጥ <u>***ማቴ 5፡42***</u>፣ ያለህን ሽጠህ ለድሆች ስጥ ማቴ <u>***19፡21***</u>፣ ያላችሁን ሽጡ ምጽዋትም ስጡ ሉቃ <u>***12፡33***</u> ብሎ ያዘዘን እምነት በመስጠትም ስለሚፈተን ነው፡፡ እንግዲህ ‹‹ነገር ግን ብልም ዝገትም በማያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በማይሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ›› <u>***ማቴ 6፡19***</u> ብሎ እንዳዘዘን በመስጠት ጸንተን ባለመስጠት የወደቅን ሆነን ከመገኘት እንጠንቀቅ፡፡

2. ሰንበትን በማክበርም መፈተን አለ፡፡ በሰንበት የእግዚአብሔርን ሥራ በመሥራት እንገኝ፡፡

3. ጸሎት በመጸለይም መፈተን ሌላው እምነታችን የሚፈተንበት መንገድ ነው፡፡ ጸሎት መጸለይን እንረሳለን፣ ስንጸልየስ ለሌላ ጉዳያችን ለመድረስ ስንል አእምሮአችን በሌሎች ሐሳቦች ይያዛል፣ በሚያነጋግረን በእግዚአብሔር ፊት መቆማችንንስ እንረሳለን? እንደዚህ ከሆነ እምነታችን ጎደሎ ነው፡፡

- ስንጸልይ የምንጸልየውን ቃል እየሰማን ከፊታችን ያለውን እያስተዋልን ከሆነ እግዚአብሔርን ደስ እናሰኘዋለን፡፡

# <u>የእምነት ሕይወት - የመጨረሻ ክፍል ፮</u>

7. **እምነታችን ለዘላለማዊ ሕይወታችን በምናደርገው ክብካቤ ልክ ይመዘናል**

- **የተወደዳችሁ ክርስቲያኖች በዚህ ዓለም እንዴት ስኬታማ ለመሆን እንደምንችል በማሰብ ብቻ የምንደክም ነን ወይስ ዘላለማዊውንም ርስት ለመውረስ ጭምር የምንጣጣር?** ‹‹ወገባችሁ የታጠቀ መብራታችሁም የበራ ይሁን፤ እናንተም ጌታቸው መጥቶ ደጁን ሲያንኳኳ ወዲያው እንዲከፍቱለት ከሰርግ እስኪመለስ ድረስ የሚጠብቁ ሰዎችን ምሰሉ ጌታቸው በመጣ ጊዜ ሲተጉ የሚያገኛቸው እነዚያ ባሪያዎች ብፁዓን ናቸው፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ታጥቆ በማዕድ ያስቀምጣቸዋል ቀርቦም ያገለግላቸዋል።›› ***<u>ሉቃ 12፡35-37፡፡</u>***
- **ዝግጅታችንም ንስሐ በመግባት፣ በመልካም ሥራ፣ በፍቅር ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት በማድረግ ነው፡፡ ይህም ዘይቱንና መብራቱን አዘጋጅቶ እንደ መገኘት ነው፡፡** ***<u>ማቴ 25፡1-13፡፡</u>***

8. **ሃይማኖታችን የጠራ እምነትን በመያዝም ይፈተናል**

- **የቀናውን ያልተበረዘውን፣ ሐሰትና ጥርጥር የሌለበትን እምነት ይዞ በመኖርና ባለመኖር መካከል መፈተን አለ፡፡** ‹‹ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ።›› ***<u>ይሁ 3</u>***፣ ‹‹ብንጸና፥ ከእርሱ ጋር ደግሞ እንነግሣለን፤ ብንክደው፥ እርሱ ደግሞ ይክደናል፡፡›› ***<u>ካል ጢሞ 2፡12፡፡</u>*** **የተባለው ስለ እውነተኛይቱ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖት ነው፡፡ ይህም የጌታችንን፣ የሐዋርያትን ትምህርት፣ ትውፊትና ሥርዓት መሠረት ያደረገ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ነው፡፡ ታዲያ ይህን እውነት እናስፋፋለን ወይስ የራሳችንን አስተሳሰብ እንደ ሃይማኖት እንሰብካለን? የቀናውን እምነት ይዞ መገኘት ሥራን ለመሥራት ይረዳል፡፡** ‹‹እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በመንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም፥ የቀደመችውንም መንገድ ጠይቁ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደ ሆነች እወቁ፥ በእርስዋም ላይ ሂዱ፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ እነርሱ ግን፦ አንሄድባትም አሉ።››***<u>ኤር 6፡16፡፡</u>***
- **የእምነት ሕይወት በሚል ርዕስ የጀመርነው የ2005 የዐቢይ ጾም ትምህርት ተፈጸመ፡፡ በኦርቶክሳዊ ተዋሕዶ ሃይማኖታችን እስከ ፍጻሜው ጸንተን በቀና ሥነምግባር በመልካም ሕይወት ለመመላለስ ያብቃን፡፡ አሜን!!!**

ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org